# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ቁጥር 4 ታህሳስ ፳፯ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## የትግል ውጤት

(ድምጽ ቅጅውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=UkBTJeaae-k)

በህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ማዕከላዊነት ሌሎች ሦስት የዘር ድርጅቶችን፦ የአማራ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)፣ የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ)ና ደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራቲክ ንቅናቄ (ደሕዴን) አካቶ እራሱን የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግምባር (ኢሕአዴግ) በማለት ሀገሪቷን ለ27 ዓመት የተቆጣጠረው ብቸኛ ፓርቲና መንግስት ታህሳስ 21 ቀን 2010 ዓ.ም. የ27 ዓመት የዘር አገዛዙን በ17 ቀን ግምገማ አስደምጦናል። በኢሕአዴግ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ ኢንተርሃሞይ፣ ሽብርተኛ፣ ፀረ-ሰላም ለመሳሰሉት የተለመዱ ቃላቱ አዲስ እንዳልሆንን ሁሉ ለሰሞኑ የኢሕአዴግ ማላገጫ ልንደነቅ አይገባም። ጩኸቱ በአጭሩ "ሕዝብ እንዴት ከእኛ በላይ ይሆናል" ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለው እንደ ኢሕአዴግ መግለጫ "ሁከትና ረብሻ" ሳይሆን መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎችን የሚያስተጋባ ሕዝባዊ አመጽ ነው። ይህ የሕዝብ እንቅስቃሴ መንግስት "በቸርነቱ የለገሰውን" ዴሞክራሲ መብቱን ጠልቶ አይደለም። ይህ ሕዝባዊ ዓመጽ የተከሰተው "ልማታዊው መንግስት" ሀገሪቷን የዳቦ ቅርጫት አድርጎ ከጥጋብ የመነጨ አይደለም። ይህ ሕዝባዊ ተቃውሞ ለ27 ዓመት በህወሀት/ኢሕአዴግ የግፍ አገዛዝ እየተንገፈገፈ ያለ መከረኛ ሕዝብ አንዴ ሞቅ፤ ሌላ ጊዜ ቀዝቀዝ እያለ እንደ እሳተ ጎመራ ዛሬ የወለደው የትግል ፍላቱ ላይ የደረሰ ሀገርና ሕዝብ የማዳን የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ ነው።

በሀገራችን የመንግሥታት ታሪክ ከዓፄዎቹ ዘመን መንግሥትነት በመዋለድ ታሪክ ወዲህ በዓፄ ኀይለሥላሴ ንጉሥነት ያከተመው ዘውዳዊ አገዛዝ በደርግ ሲተካ፣ ደርግ በወያኔ ሲተካ ተመሳሳይ ሂደቶች ታይተዋል። በዓፄው አገዛዝ በመላዋ ሀገሪቷ የተነሳው ሕዝብ "ራበኝ፣ ጠማኝ፣ በረደኝ፣ አመመኝ፣ ደነቆርሁ፣. . ." ብሎ ነው። ሀገሬ ለእኔ ብሎ "ያረስኩትን ልብላ፣ የወለድኩትን ላስተምር፣ ልጓሜ ይፈታልኝ" ያለ ሕዝባዊ አብዮት ነው የዘውድ አገዛዝን ለአንዴም ለመጨረሻ የገረሰሰው። የተነሱትን ሕዝባዊ ጥያቄዎች ለሥልጣን መወጣጫ የተጠቀመበት ወታደራዊው የደርግ አገዛዝ የሀገሪቷን ችግሮች ይብስ አወሳስቦ በጥይትና ቦምብ ለመፍታት ያደረገው ወታደራዊ ግንባታ ከሕዝብ ጥያቄ አልበለጠምና ትውልድ አውድሞ በወያኔ ተተክቷል። 17 ዓመት በደርግ ላይ በነበረው ምሬትና ስቃይ እየተብላላ የመጣው የሕዝብን ስቃይና መከራ ተገን በማድረግ ለአንድ ጎሳ ነጻነት "የትግራይ ነፃ አውጪ" ብለው የተነሱት ህወሓት መደራጀት፣ መታጠቅ ጥቅም አለውና የኢሕአዴግን ካባ ለብሰው የምኒልክን ቤተ መንግሥት ለመቆጣጠር ችለዋል።

ኢሕአዴግ/ህወሓት በ27 ዓመት አገዛዙ ሀገርን በቋንቋና በዘር በመከፋፈል ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትን ለመሸርሸር ያደረገው ተንኮሉ፣ የሀገሪቷን ለም መሬቶችና የማዕድን ክምችቶች ለጥቂት

ቱጃሮችና የውጭ ዘራፊዎች አሳልፎ በመሸጥ የሀገሬውን ነዋሪ አውላላ ሜዳ ላይ ጥሎ በማላገጡ፣ በዝርፊያና በሙስና የሀገር ሀብት በማራቆት፣ ጥሮ ግሮ አዳሪ ምስኪኖችን ጎጆ በመደርመስ ለጎዳናና ለላስቲክ ቤት ተዳዳሪ በማድረግ ሕፃናት ልጆቻቸውን ለልመና፣ የደረሱች ሴት ልጃቸውን ለሴተኛ አዳሪነት፣ ወጣት ወንዶችን ለወያላነት፣ ቦዘኔነት፣ በጊዜው ቋንቋ ለፍንዳታ፣ ከዚህ ያመለጡትንም በስደተኝነት መልክ በመቸብቸብ በባህር ከመስጠምና በአውሬ ከመበላት የተረፉትን በተለይ በአረቡ ዓለም ለአስከፊ ስቃይ በመዳረግ ቤተሰብንና ሀገርን ያስለቀሰ አገዛዝ ውጤት ነው ዛሬ ወያኔ/ኢሕአዴግን ሊውጠው የተነሳው።

እውን ለመናገር ወያኔ/ኢሕአዴግ የትኛው ትህትናው ነው የተመዘገበው? የትኛው አስተዋይነቱ ነው ከተመልካች የደረሰው? የትኛው ድምጹ ነው ከሕዝብና ሀገር የተገናኘው? እና ነው ስለ ስህተትና ስለ ይቅርታ የሚደሰኩረው። ሰንደቅ ዓላማ ሲሉት ጨርቅ፣ የታሪክ ቅርስ ሲሉት ድንጋይ፣ ሀገር ሲሉት ዘር፣ ምርጫ ሲሉት ኢንተርሃሞይ፣ መብት ሲሉት አጋዚ፣ ትግል ሲሉት አሸባሪ፣ ተቃዋሚ ሲሉት አፋኝ፣ ዕርቅ ሲሉት ማን ተጣላ፣ . . . መገለጫዎቹ ናቸው፤ ሲጀመር ጀምሮ ለ27 ዓመት አብረውት የተጓዙት።

ሕዝባዊ ትግልን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ በእስር፣ በግርፊያ፣ በግድያ በማሸመድመድ ለጥቂት ጊዜ ዕድሜ ይገዛ ይሆናል፤ ሁሌም ግና አይሠራም። በቁሙ እየታሠረ፣ እየተገረፈ፣ እየሞተ ያለ ሕዝብ እውን ቀረርቶና አዋጅ፣ መግለጫና ማስመሰል አይገታውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ረሀቡን ችሎ፣ ተደብድቦ፣ ልጆቹን ገብሮ የመጨረሻው ሰዓት ከመጣ ድሉን ቢቀማ እንኳ የጠላውን ሳያስወግድ ወደ ኋላ እንደማይል ያለፉ የትግል ታሪኮቹን መቃኘት በቂ ነው። የኢሕአዴግ የሰሞኑ መግለጫ ሊበሉት ያሰቡትን ሕዝባዊ ትግል በተሳስተናልና በይቅርታ ጥይት ለመደብደብ መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ይጠይቃል። "የጨነቀው ..." እንዲሉ ወያኔ ለዓመሉ በስህተት ያላግጣል፣ በይቅርታ ያሾፋል። የመጨረሻው ሰዓት የወያኔ መውደቂያ፤ የሕዝብ መምጫ ነውና በይቅርታ የታጀቡ አደናጋሪ ጥይቶችን ነቅተን መጠበቅ ይኖርብናል። ዛሬ ለወያኔ እየጠለቀች ያለችው ጀምበር በምሥራቅ አፍሪካ ለኢትዮጵያና ሕዝቧ ብቅ ልትል ጉዞ ላይ ነች። ለወያኔ ሲጨልም ለሀገራችንና ሕዝባችን ብርሃን ይሆናልና።

27 ዓመት በጉልበትና በኃይል የገዛ የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ዛሬም ስህተታችንን አርመን እንገዛ ሲል እፍረት የለውም። የኢሕአዴግ መግለጫ

*"ህገመንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ያስከበራቸውን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የመጣስ አዝማሚያዎችና ተግባራት በጥብቅ እንዲመከቱ ወስኗል፡፡"*

ሲለን ዛሬም ሕዝባዊ ትግሉን ለማፈን አጋዚ ሠራዊቱ "ግ…ራ! ቀ…ኝ!" እያለ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል።

የህወሓትን እኩይ ተግባር ቢረዱም አቅምና ጊዜ እየጠበቁ ላሉ ሕዝባዊ ወገኖች በተለይ ወያኔ እንደሚፈልገው ዘርን ያማከለ የእርስ በርስ ፍጅት ውስጥ እንዳይገባ የምታደርጉት ጥረት የሚናቅ አይደለም። በኢሕአዴግ ውስጥም ሆናችሁ የኢትዮጵያ አንድነት እንዳይናጋና የለውጥ ሂደቱ ሰላማዊ ይሆን ዘንድ ድምጻችሁን የምታሰሙትን አበጃችሁ፣ ግፋበት እንላለን። የጋራ ሀገራችንን በጋራ እንጠብቃት ዘንድ ዋናው ጠላታችን ወያኔ ላይ አተኩረን ዘረኛ አገዛዙን ብሔራዊ ስሜትን ወደ ተላበሰና የሁላችንም የሆነች፣ የዜግነት መብት የተከበረባት ዴሞክራሲያዊ ሀገር ለመተካት መዘጋጀት ይኖርብናል ስንል ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** መልዕክታችን ይሆናል።

**በተቀጣጠለው ክልላዊና ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ትግሉ አቅጣጫውን እንዳይስትና የወያኔ አገዛዝ ያንገፈገፋቸው አንዳንድ ሚድያዎች በተለያየ መልኩ ሕዝባዊ ብሶትን ማስደመጣቸው የቆጠቆጠው ወያኔ አሁንም የአፈና እጁን ለመዘርጋት ካለው ድፍረት በሰሞኑ መርዘኛ መግለጫው ይህንን ያስነብባል፦**

*"ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በክልልም ይሁን በፌዴራል ያሉ የህዝብ የሚዲያ አውታሮች ሕግና ሥርዓትን ጠብቀው የማይሠሩበት ሁኔታ እያመዘነ የህዝቡን ሰላምና አብሮ የመኖር ገንቢ ባህል የሚሸረሽሩ ሰበካዎች የሚሰጥባቸው፣ ብሎም ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጩ አጥፊ ቅስቀሳዎች የሚካሄድባቸው እየሆኑ ለመምጣታቸው የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚም ሆነ የሚመራው መንግሥት ድክመት አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይቀበላል፡፡"*

**ለወያኔ ያልወገነ ቅስቀሳ፣ ኢ.ሕአዴግን ያላወደሰ ቅስቀሳ በህወሓት አባባል ሕዝብን ከሕዝብ ሳይሆን ወያኔን ከሕዝብ ማጋጨት ያለበትና እሰየው የሚያሰኝ የተጀመረው ፀረ-ወያኔ እንቅስቃሴ የትግል ውጤት ነው።**

**የኢ.ሕአዴግ መግለጫ ዋናው አንኳሩ አሁንም የተጀመረውን ትግል እንዴት ማሽመድመድ እንደሚገባ ለማስገንዘብ መሆኑን ከመግለጫው ይህንን ደግመን በማስነበብ እናሳያለን።**

*"በልማትና በሃገራዊ አንድነት ዙሪያ መትጋት ሲኖርባቸው ሕዝብን ከህዝብ ጋር በሚያራርቅ አፍራሽ ተግባር ውስጥ የተሰማሩ የግልና የመንግሥት የሚዲያ ተቋማት አካሄዳቸውን የሚያስተካክሉበት ሁኔታ ለመፍጠር እንደሚንቀሳቀስ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የወሰነ ሲሆን በተለይም በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ከፖለቲካዊ፣ ከሕጋዊ አሠራርና ከሕገመንግሥታዊ ሥርዓት በራቀ መልኩ የሁከትና የግርግር መልእክት በህዝብ ሚዲያ የሚሰበክበትን እድል ለመዝጋት የሚያስችሉ የተቀናጁ እርምጃዎችን እንደሚወስድ በዚህ አጋጣሚ ይገልፃል፡፡"*

**እንደ መግለጫው አባባል በዚህ አጋጣሚ ልንገልጽ የምንወደው ትግሉ ሕዝባዊ አጀንዳ መያዙን ያልተቀበለ አገዛዝ ትግል ሲሉት ሁከት፣ ግርግር ነውና መልሱ እኛም መግለጫውን "የጣር ጩኸት፣ የሽንፈት ምልክት" ብለን ትግሉን ከድል ለማብቃት መቁረጥ ይኖርብናል።**

**አንዳንድ የክልል መገናኛ ብዙኃን በመካሄድ ላይ ያለውን አካባቢያዊ እንቅስቃሴ አስመልክቶ የምታደርጉት ቀናና ሕዝባዊ ወገንተኝነት ያስደነገጠው ህወሓት፤ በተለይ የአማራና ኦሮሞ ክልል ሚድያዎችን ይበልጥ ለማፈን እንደተዘጋጀ የኢ.ሕአዴግ መግለጫ ቢያስገነዝብም ጥረታችሁና ትግላችሁ ለሀገርና ህዝብ ነውና ግፉበት እንላለን።**

**የንጉሡ አገዛዝ በየካቲት 66 ሕዝባዊ ማዕበል ሲዋጡና የትግሉ ማቆሚያው የሥርዓቱ መውደቅ ብቻ መሆኑን ከመረዳት ይልቅ "ፋታ ስጡን" እያሉ ልጅ እንዳልካቸው ቢ.ማጸኑ አልሆነም። ሥርዓቱ ሀገሪቷን ለመቀየር ያለውን ዕድል በተለይ ከ1953 ዓ.ም. የታህሳሱ መፈንቅለ መንግሥት ወዲህ ለምን? ምን ማድረግ አለብን? ብሎ በርካታ ጉዳዮችን መቀየርና ማሻሻል ሲቻል የተያዘው ለዘብተኝነትና የሚነሱ ጥያቄዎችን አለማድመጥ ከ13 ዓመት በኋላ ለከፋ አወዳደቅ ሥርዓቱንም ባለሥልጣናቱንም ዳርጓል።**

**ሲጀመር ጀምሮ ሀገሪቷን በግድያና በጦርነት የዘፈቀው ደርግ ለሥልጣኑ ሲል አንድ ትውልድ እምሽክ አድርጎ እርካታ አላገኘም። በሀገሪቷ ያሉ እንቅስቃሴዎችን በእርጋታና በምክክር ለመፍታት ከመጣር ይልቅ ሀገሪቷን ለአንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን አሳልፎ የመጨረሻው ሰዓት ላይ የራሱንና የሀገሪቷን እውቅ የጦር መኮንንኖች ሳይቀር የበላ አገዛዝ ነበር። ይህ ሁሉ በሰው ልጅ ደም ጨዋታ ፀፀትን ለሀገር አተረፈ እንጂ ደርግን ከ17 ዓመት በላይ ዕድሜ አልሰጠውም። በግድያና በንፁሐን ደም ማፍሰስ ቢሆን እንደ ጀርመኑ አዶልፍ ሂትለርና እንደ እኛ መንግሥቱ ኃይለማርያም ዕድሜ ልክ የሚገዛ አይኖርም ነበር። በመጨረሻም ያ ቀና ተብሎ የማይታይ ፋሽስት መሪ በምክር ቤት ተዋርዶ "አንድ ሰውና አንድ መሳሪያ" እንዳለው እራሱንና የታጠቀውን ሽጉጥ ይዞ ፈርጥጧል።**

*አምባገነኖች የአንድ ሳንቲም ገጽታዎች ናቸውና የጊዜው ወያኔ/ኢሕአዴግም እጣ ፋንታው ከዚህ አይዘልም። መንግሥት ይመጣል፣ መንግሥት ይሄዳል አምባገነኖች ላይ ሲደርስ እውን ይሆናል። ህወሓት በተለያየ አጋጣሚ ከሀገርና ሕዝብ ጋር ሊታረቅ የሚችልበትን አጋጣሚ በእብሪትና በማን አህሎኝነት የናቀ አገዛዝ ነው። በ1993 ዓ.ም. ህወሓት ሲከፋፈል የወቅቱ ጠ/ሚንስትር "በስብሰናል፣ ተጨማልቀናል፣..." ማለሳለሻ ዲስኩራቸውን ወደ ሀገርና ሕዝብ መመልከቻ ቢያደርጉት ዛሬ ዳግም "ተሳስተናል፣ ይቅርታ. . ." እየተባለ ባልተሾፈ። በቀጣይነት በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ድል የተቀዳጀውን የሕዝብ ኃይል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆ "ጣት እንቆርጣለን" ፉከራና የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘም የተደረገ የንፁሐን ደም ማፍሰስ ለዛሬው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አስተዋጽዎ እንዳለው አለመገንዘብ በመሳሪያቸው የተማመኑ አገዛዞች ባህሪ ነው። ህወሓት በተደጋጋሚ የቀረበለትን የሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ ጥሪ "ማ ከማ ተጣላ?" እያለ ሲያላግጥ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። ገና ከጅምሩ የኢትዮጵያ የሰላምና ዴሞክራሲያ አማራጭ ኃይሎችን ጥረት በእሥር የለወጠ አገዛዝ ለመሆኑ ተግባሩ ምስክር ነው።*

*በዚህ ዘገባችን በአንድ በኩል ሕዝብን ማድመጥ ያልቻለ አገዛዝ አወዳደቁ አስከፊ እንደሚሆን ስናሳይ በሌላ በኩል ወያኔ/ኢሕአዴግ በሰሞኑ መግለጫውም ሆነ በማግስቱ በጠ/ሚንስቴሩ ኃይለማሪያም ደሳለኝ የተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በሀገሪቷ የተለያዩ አካባቢዎች የሚደረጉት ትግል ውጤት ነውና መፍትሄው የተጋጋለውን አካባቢያዊ ትግል ሕዝባዊ መልክ አስይዞ ለድል በማብቃት ይህ ዘረኛ ሥርዓት በነበር ይታወስ ዘንድ መሥራት ይጠበቅብናል።*

*መውደቂያው የተቃረበው ህወሓት/ኢሕአዴግ ለሕፃን ልጅ "ከረሜላ እንድሰጥህ. . ." ዓይነት ሹፈት ይዟል። ጠ/ሚንስትሩ "ማዕከላዊን ዘግተን ሌላ በአዲስ መልክ እንከፍታለን" ይሉናል። አጀብ! ያሰኛል። መጪዋ ኢትዮጵያ በፖለቲካ አቋምና በአስተሳሰብ ልዩነት የዜጎቿ እስር ቤት እንደማትሆን ጠ/ሚንስትሩ ሊገነዘቡት ይገባል። መፍትሄው ሌላ ማሰቃያ እስር ቤት ሳይሆን የዴሞክራሲን በር መክፈት ነው። "የፖለቲካ እስረኛ የለንም" እያለ ያላገጠ መንግስት ዛሬ ደግሞ "የፖለቲካ እስረኞች ይፈታሉ" ሲሉ ያ ሁሉ አጋዚ፣ ያ ሁሉ ጥይት፣ ያ ሁሉ ታንክ፣ ያ ሁሉ ሰላይ፣ ያ ሁሉ 1 ለ 5 ጥርነፋ፣ ያ ሁሉ አዋጅ፣. . . ከሕዝብ በላይ እንዳልሆነ መስካሪ ነው። የመጨረሻው ሰዓት እውንም ከባድና አስቸጋሪ ነው። "ጉም መጨበጥ፣ የፈሰሰ ውሃ. . ." ይሉታል ይሄ ነው።*

*"ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታት" ጉዳይ መተግበር እንዳለበት በህወሓት አገዛዝ ለ27 ዓመት ትግል ተካሂዶበታል። የሁሉንም መፈታት እንፈልገዋለን። ይህ ከመሠረታዊ ጥያቄዎች እጅግ አንዱ ነው። ወያኔ ሊመልሳቸው የሚገባቸው በርካታ ጥያቄዎች ዛሬ ትግል ሁነው ዘረኛውን አገዛዝ መጨረሻው ሰዓት ላይ አድርሰውታል።* ***<u>ዛሬ ጥያቄዎቹ የሀገርና የሕዝብ ህልውና ብሎም የህወሓት ሥርዓት ማክተም ሆኗል።</u>*** *ለህወሓት ዕድሜ በመስጠት አብረን ትንሽ ሀገርና ሕዝብ እንቦጥቡጥ ካልሆነ በቀር አገዛዙ ዝናብ አይፈራምና መወገድ ያለበት ነው።*

*ምክር ሰሚ ከሆኑ ህወሓት/ኢሕአዴግ ዛሬ አንድና አንድ ምርጫ አላቸው። በ27 ዓመት የአገዛዝ ዘመናቸው ገና ጥቂት የወያኔ ቡድን አባላት የሚያውቁት ለሕዝብ ግልጽ ያልሆነ ግፍና በደል በሀገርና በሕዝብ ላይ ሠርተዋል። ኢትዮጵያን ታሪኳንና ቅርሶቿን ዘርፈዋል። ወደዱም ጠሉም ሀገርና ሕዝብ አስለቅሰዋል፣ አቁስለዋል፣ አድምተዋል። ለዚህ ሁሉ አድራጎት "ተጠያቂነት" የሚሉት ከባድ ቃል አለ። አውላላ ሜዳ ላይ የተወረወሩ፣ ቤታቸው የተዘጋ፣ ሕይወትን ከረሃብ ጋር የተጋፈጡ፣ "ሞቴን አቅርብልኝ" ባይ የወያኔ ሰለባዎች በሚልዮን ይቆጠራሉና ስለ ፍርድ "እግዚዮ!" ይላሉ። ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ ዜጎቻችን የስውር ዘር ማጥፋት ሰለባዎች ከንፈር ተመጦ ዝም የሚባል አይደለም። የሰውን ልጅ ደም አስለቅሰው፣ በሀገርና ሕዝብ ሀብትና ንብረት ዛሬ ቱጃር የተባሉ ዘራፊዎች አላግባብ ብልጽግና ይጠየቃሉ። ይህ እጅግ ከብዙው ጥቂቱን ለማንሳት ነው። ይህ መሬት ላይ ያለው ሀቅ ነው።*

**ወያኔ "እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ አበቃላት" ተረቱን ይቅበረውና የአገዛዝ ዘመኑ እንዳበቃለት ተገንዝቦ ያለምንም ማቅማማት ሥልጣኑን ለሕዝብና ለሀገር በሰላም ያስረክብ ዘንድ የመጨረሻ ዕድሉን ይጠቀምበት እንላለን። አዎ! ይህ ኢትዮጵያ ላይ ከወያኔ ሌላ በሌሎችም ሊያንዣብብ የሚችለውን አደጋ ያስወግዳልና። ዛሬ የአማራውና የኦሮሞው ትግል በጋራ ህወሓት ላይ ማነጣጠሩ ሳይውል ሳያድር የትግራይ ልጆችም እንደሚቀላቀሉት አትጠራጠሩ። እርስ በርስ የማፋጀት ፈንጂው ከሽፏልና የህወሓት አለመኖር ለኢትዮጵያ አንድነትና ደህንነት እንደውም ተፈላጊነቱ ከወዲሁ እየታየ ነው። በሰሞኑ የኢሕአዴግ መግለጫ ይቅርታው በሥልጣን ለመቆየት ሳይሆን ለመልቀቅ ቢሆን ያላችሁን በጎና ቅን አማራጭ እንደተጠቀማችሁበት ለማስገንዘብ እንወዳለን። በሕዝብ የበላይነት ካመናችሁ ያለምንም ማቅማማት ብሶቱንና ድምጹን አድምጡ። የዚህ ጊዜ ይቅር ባዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ እናንተንም ይመለከታል።**

**ከዚህ በዘለለ በቀጣይ ሂደት በፌደራልና በክልል ያለውን የፖሊስ ሠራዊትና አጋዚ ጦራችሁን በአንድ የህወሓት ዕዝ ሥር አድርጎ የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ ትግል ለማኮላሸት በተደጋጋሚ እንደተደረገው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሙከራዎች ለመቀጠል ከታሰበ ህወሓት/ኢሕአዴግ የትም እንደማይደርስ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የአገዛዝ ጊዜያችሁ አብቅቷል። ልታደርጉ የምትችሉትን ወያኔያዊ ኃይል በተደጋጋሚ ተጠቅማችሁ የንፁሃንን ሕይወት ቀጥፋችኋል። ዛሬ ግን የመጨረሻው ደውል ለናንተ ነው። ሰው ሊኖር ሰው ሞቷል፣ ሀገር ልትኖር አጥንት ይከሰከሳል፣ ደም ይፈሳል እንጂ እውነት . . . እውነት እንላችኋለን የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝና ሥርዓት አብቅቶለታል።**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!**
**"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"**
**ታህሳስ 27 ቀን 2010 ዓ.ም. (January 05, 2018)**

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማኒፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin